# ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተሰጠ መግለጫ

ከመስከረም 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ አሮጌውን ብር በአዲስ የብር ኖቶች እየቀየርን መሆኑ ይታወቃል፡፡ አሮጌውን ብር የመቀየር ሥራ በሶስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ መወሰኑ ይታወሳል፡፡ እስካሁን ባለው የብር መቀየሩ ሂደት በተሳካ ሁኔታ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ሆኖም ግን አሮጌ ብር በአዲስ ብር የመቀየሪያው የመጨረሻ ቀን ታህሳስ 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ነው፡፡ ከዚህ ቀን በኋላ አሮጌ ብር በባንኮች አይቀየርም፡፡

በመሆኑም የተፈቀደው የብር መቀየሪያ ሶስት ወራት ሊጠናቀቅ 25 ቀን ቀርቶታል፡፡ በቀሪዎቹ ቀናቶች ያልተቀየረ ብር እንዲቀየርና ሂደቱን ለማፋጠን ከህዳር 22 ቀን 2013 ዓ.ም. እስከ ታህሳስ 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ባሉት 15 ቀናት በአሮጌ ብር ግብይት መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡ ግብይት በአዲስ ብር ብቻ ይሆናል፡፡ በእነዚሁ የመጨረሻዎቹ 15 ቀናት ማንኛውም ሰው አሮጌውን ብር ወደ ባንክ ሂዶ መቀየር ግን ይችላል፡፡

ታህሳስ 6 ቀን 2013 ዓ.ም. የመጨረሻው የብር መቀየሪያ ቀን መሆኑ ታውቆ ህብረተ-ሰቡ በእጁ ያለውን አሮጌ ብር እንዲቀይር በድጋሜ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡ የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ አስተዳደር እና የፀጥታ አካላትም ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የበኩላችሁን ድርሻ እንድትጫወቱ እንጠይቃለን፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ!

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA